# ይኸው ነው መልዕክቴ!

በሰው ሀገር ምድር በስደት ላላችሁ፣
ለሀገሬ ልጆች፣ ስሙኝ ልንገራችሁ፣
ምንም ሳይዋረድ ሰብዓዊ ክብራችሁ፣
መኖር እንድትችሉ በሥራ ኮርታችሁ፣
ከአገር የበለጠ መቼም የትም የለም፣
ዓለምን ብትዞሩ እስኪነቃ እግራችሁ!
ውሎና አድሮ ነገ፣ ሁሉም ሲገባችሁ፣
አይቀርም አንድ ቀን፣
የነገ ራዕይዋን እውን ማድረጋችሁ፡፡

ግን እስከዚያ ድረስ መጠበቅም ሳይኖር፣
ነገ ሳይሆን ዛሬ መስራትን ብንጀምር፣
ድህነትን ከሀገር ማጥፋት እንችል ነበር፡፡
ጠመዝማዛው መንገድ፣  የተጓዝንበት፣
ውጣ ውረድ ያለው ዳገት ቁልቁለት፣
ምቹነትን ፈጥሯል፣ አምጥቷል ውጤት፡፡
አሁን ያለንበት፣ የደረስንበት፣
እልፍ አዕላፍ ዘመን የተለፋበት፣
መንገዱ ምቹ ነው፣ ለማምጣት ዕድገት፡፡

የአገሬ ልጆች እስኪ አስቡበት ፣
እማማ ኢትዮጵያ የፍቅር ደሴት፣
ተፈጥሮያዊ ሀብቷን ልጆቿ እያዩት፣
ጥለው ኮበለሉ፣ናፍቋቸው ስደት፡፡

ምንም ያልተነካ፣ እምቅ ኃይልን ይዞ፣
ወደ ስደት መንደር ፈቷን አጠማዞ፣
ስደት በመናፈቅ የጀመረው ጉዞ፣
ወዴት ነው መድረሻው ማለቂያው ተግዞ ፡፡

ከወዴትስ ይምጡ አንችን የሚያለሙት፣
ልጆችሽ ከሆኑ ስደት ‘ሚናፍቁት፣
በዕድሜ ደረጃቸው የሆኑት ወጣት፡፡

ሀገር ማለት ሰው ነው፣ ሰው ነው የሀገር ሀብት፣
ይህንን ማስተዋል፣ እንዴት አጡበት፣
አቅጣጫውን ስቶ የህይወት መስመሩ፣
ቀርቷል ባገር መኩራት ሆኖበት ነውሩ፣
ስደት ብቻ ሆኗል፣ የሌት ተቀን ህልሙ፣
ተስፋው ተሟጦበት ሳይሰራ መድከሙ፡፡

መቅኖ ባጣ ህይወት በተቅበዘበዘ፣
ተስፋው ተሟጦበት ቀረ እንደፈዘዘ፣
ቀረ እንደተከዘ፤
ዛሬም አላቆመም አለ እንደተጋዘ!!

# ከቶ ማን ነህ አንተ?

ያደራ ቃል ኪዳን፣ የተረከብከውን፣
ከምን አደረስከው፣ የእናት አገርህን፤
ተስፋዬ ነው ብላ ለምትጠብቅህ፣
ለእማማ ኢትዮጵያ ለውዲቷ አገርህ፣
ከቶ ምን ሰርተሀል፣ ምንስ ነው ሀሳብህ፣
ምን አስተማርካቸው ለተከታዮችህ፣
ለታናናሾቹ
እህት ወንድሞችህ፡፡

ለተከታዮችህ እንካችሁ ‘ምትለው፣
አደራዬ ብለህ የምትሰጣቸው፣
ከቶ ምን አሻራ አለህ?
ምታስረክባቸው፤
አገርን ማልማት ነው፣ ወይስ ስደትን ነው፣
ካለፈ እንዳይቆጭህ ቆም ብለህ አስበው፡፡

እስኪ አስብ ቆም ብለህ የቱጋ ነው ያለህ
አቋምህ ምን ይሆን ምንስ ታስባለህ?

ይልቅ ታጥቀህ ተነስ፣ ስደቱ ቀርቶብህ፣
ሰርተህ ለመለወጥ በአገር በምድርህ፣

አርዓያ ለመሆን ለታናናሾችህ
ለእህት ወንድሞችህ፣
ጊዜው ጥሎህ ሳይሄድ እውን ይሁን ህልምህ፡፡

ሌሎች እንዲመጡ ወደ አገራቸው፣
አርዓያ በመሆን ሥርተህ አሳያቸው፤
ስምህ እንዲነሳ  በመልካም አብነት
ቀርቶብህ ወቀሳ፣
ነገ ዛሬ ሳትል
ሰርተህ ለመለወጥ
ክንዶችህን አንሳ!!

ይርጋለም ደጄኔ
(ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር)